# በኢትዮጲያ ስም አይነገድም!

## አገር ወዳድ ኢትዮጲያውያን የወያኔን ባለሟሎች ለማሳፈር እንዘጋጅ

ግፍን፣ ስቃይን፣ረሃብንና መከፋፈልን በህዝባችን ላይ አስፍኖ ስርቆትንና ሙስናን ዋናው ትግባሩ ያደረገው የመለሰ ማፊያ ቡድን ባልፉት ሃያ-ዓመታት ተግባሩ ኢትዮጲያን በዓለም 2ኛ ድሃ አገር፣ በትምህርት ዘርፍ ደግሞ ከመጨረሻዎቹ 5ኛ ሲያደርጋት፣ ይሄው ቡድን ሰባዊ መብትን በመጣስ፣ ነፃ ጋዜጠኞችን በማሰርና በመግደል፣ በሙስናና በስርቆቱ በዓለም የቀዳሚዎችን ስፍራ ይዟል።

ዛሬ ሕዝባችን በወያኔ የግፍ ስርዓት ሥር ሊገለጽ በማይችል የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማህበራዊ አዝቅጥ ውስጥ ወድቋል።

- የወያኔን ስራዓት እድሜ ለማራዘም ታስቦ የተነደፈው የመለሰ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የሕዝብን ሃብትና ንብረት እንዲሁም በርሃብተኛው ስም የሚለምነውን ገንዘብ ጠቅልሎ በመለሰ፣በሚስቱና በጥቂት የወያኔ አጫፋሪዎች እጅ አስገብቶታል።

- የነፃ ገበያ ሕግጋትን በመፃረር ዋና-ዋና የሚባለው የኢኮኖሚ ዘርፍ ጥቂት የወያኔ መሪዎች በመዳፋቸው አስገበተው የቀሪውን የኢትዮጲያ ሕዝብ አበሳውን እያሳዩት ነው።

በኢንቨስትመንት ስም፦

መለሰ የኢኮኖሚ ጠበብቶችን ምክር ረግጦ የብርን ዋጋ ያለ አግባብ በመጣል፣ 80 ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርበትን አገር ወደብ-አልባ በማድረጉ ምክንያት ከውጪ በሚገቡ የሸቀጦች ዋጋ መናርና የተረጋጋ ነፃ-ገበያ እንዳይኖር ሙስናን አስፍኖ ሕግ-አልባ የገበያ ማፊያዎችን አሰማርቶ ኢትዮጲያን ጉርሻ የሚሸጥበት፣ ለስኳርና ለዘይት ሕዝብ ለ8 ሰዓት የሚሰለፍበት፣ እናቶች ቡና መቅመስ ያልቻሉበት፣ ወጣቶች በርሃብ-ጠኔ በጎዳና ዳር ደርቀው የሚገኙበት አገር አድርጓታል።

በኢንቨስትመንት ስም፦

በገጠር የሚኖረው ወጣት አርሶ የሚበላው መሬት ተነፍጎት ለከተማ ርሃብ ሲዳረግ የህግራችን ለምና ድንግል መሬት ግን ወያኔ ለአረብና ለኤሲያ ቱጃሮች በርካሽ እየቸበቸበ ገንዘቡን ወደ ውጭ ማሸሹን ተያይዞታል።

በኢንቨስትመንት ስም፦

በከተማም ድሃው ሽጦና ለውጦ ከሚያድርበት ቀዬው መለሰ በግሬደር እየጠረገው ለወያኔ ሹማምንትና ለቤተሰቦቻቸው እየተሸነሸነ ሲታደል፤የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ (VOA) በ 3/21/11 እንደዘገበው ቤቱ በላዩ ላይ የተናደበት ወላጅ የወያኔን ባለስልጣን "ልጆቼን ምን ላርጋቸው"? ብሎ ሲጠይቅ የተሰጠው መልስ "ማን ውለድ አለህ"? የሚል ነበር።

በኢንቨስትመንት ስም፦

የእስከዛሬው ግፍ አልበቃ ብሎአቸው ከመለሰ የተላኩ ቡችሎች አይናቸውን በጨው አጥበው እነሆ ከተማችን ድረስ መጥተው ስለ ኢንቨስትመት ተረት ሊያወሩ በከተማችን ከሚገኙ ሆድ-አደሮችና በወገናቸው ስቃይ ላይ መበልጸግን ከሚመኙ ህሊና-ቢሶች ጋር ሊነጋግሩ በ April 10 ቀጠሮ ይዘዋል። ይህንን ሴራ ለማክሸፍ ሀገር ወዳድ ኢትዮጲያውያን በእለቱ በታላቅ የህዝብ ቁጣ በታጀበ የተቃውሞ ሰልፍ የስብሰባ ቦታቸውን ለማጥለቅለቅ ቆርጠው ተዘጋጅተዋል።

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የዚህን አስከፊ አገር-አፍራሽ፤ ትውልድ-ገዳይ ቡድን የስብሰባ ጥሪ የደረሳችሁና ወያኔን ለማጀብ ለምትቋምጡ ሁሉ ሰልፋችሁን ከህዝብ ጎን ማድረግ ከውርደት ያድናል ብለን እናስጠነቅቃለን!

በሳን-ፍራንሲስኮ ባህረ-ሰላጤ የምንገኝ አገር ወዳድ ኢትዮጲያውያን በሙሉ በዚህ እለት ወጥተን በሰልፉ ቦታ በመገኘት የወያኔን የግፍ ስርዓት በማጋለጥ ለወገናችን አጋርነታችንን እንድንገልጽ ጥሪ እናደርጋለን።

**በእኛ ስም አይነገድም !**

**የሕዝባችን ንፃነት ቀኑ ቀርቧል!**

**ድል ለኢትዮጲያ ህዝብ !**

ከአገር ወዳድ ኢትዮጲያዊያን።